መልእክት ሁለት

**እስከ ብስለት በሕይወት በማደግ**
***ለጌታ መምጣት ራሳችንን ማዘጋጀት***

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ዕብ. 6፡1፤ ኤፌ. 4፡13፤ ቆላ. 1፡27-29፤ 4፡12፤ ራእ. 14፡1-5

**I. *ያዕቆብ በመልእክቱ፣ የከበረውን የመሬት ፍሬ በትዕግሥት የሚጠብቅን ገበሬ ምሳሌ ይጠቀማል—5፡7፦***

ሀ. ጌታ ኢየሱስ በእርግጥ እውነተኛው ገበሬ፣ ልዩና ብቸኛው ገበሬ ነው—ማቴ. 13፡3።

ለ. የጌታን መምጣት በትዕግሥት ስንጠባበቅ ሳለ፣ እርሱ እንደ እውነተኛው ገበሬ፣ እንደ በኩራትና የእርሻ መከር በሕይወት መብሰላችንን በትዕግሥት እየተጠባበቀ ነው—ራእ. 14፡4፣ 14-15።

ሐ. “ጌታ ሆይ፣ በቶሎ ና” ብለን ከጸለይን፣ ጌታ “የኔን ተመልሶ መምጣት ስትጠባበቁ ሳላችሁ፣ የእናንተን ብስለት እየተጠባበቅሁ ነው፤ ተመልሶ መምጣቴን ማፋጠን የሚችለው የእናንተ ብስለት ብቻ ነው” ሊል ይችላል።

መ. የጌታን ተመልሶ መምጣት መጠባበቃችንን እንደ ቁም ነገር ከያዝነው፣ እስክንበስል ድረስ በሕይወት ማደግ እንደሚያስፈልገን መገንዘብ ታላቅ እርዳታ ነው።

**II. *መብሰል ክርስቶስ በውስጣችን መሠራቱ ነው—ገላ. 4፡19፦***

ሀ. በክርስቶስ ባመንን ጊዜ እርሱ በውስጣችን ተወለደ (ዮሐ. 3፡6፣ 15-16)፣ በክርስትና ሕይወታችን እርሱ በእኛ ይኖራል (ገላ. 2፡20)፣ ስንበስል እርሱ በእኛ ውስጥ ይሠራል (4፡19)፦

1. የልውጠት የመጨረሻው ደረጃ ብስለት፣ የሕይወት ሙላት ነው፦
   ሀ. የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዓላማ ሊከናወን የሚችለው በመለወጣችን እና በመብሰላችን በኩል ብቻ ነው—ዘፍ. 1፡26፤ ቆላ. 1፡28፤ 2፡19፤ 4፡12።
   ለ. ብስለት የሕይወት ሙላት እስኪኖረን ድረስ መለኮታዊው ሕይወት ደግሞ ደጋግሞ ወደ እኛ ውስጥ የመተላለፉ ጉዳይ ነው—ዮሐ. 10፡10።
2. ብስለት የአቅም መተለቅ ጉዳይ ነው—መዝ. 4፡1፦
   ሀ. በሕይወት መብሰል የመንፈስ ቅዱስን ቅጣት የመቀበል ጥቅል-ድምር ነው—ዕብ. 12፡5-11።
   ለ. ሌሎች በሕይወት የበሰለን ሰው ያዩ ይሆናል፣ ያ ሰው በዓመታት ውስጥ በምሥጢር የተቀበለውን የተከማቸ የመንፈስ ቅዱስ ቅጣትን ግን ማየት አይችሉም—2 ቆሮ. 1፡8-10፤ ዘፍ. 47፡7፣ 10።
3. በእግዚአብሔር ለመሞላት የጨመረ አቅም ይኖረን ዘንድ ከሞሉን ነገሮች ሁሉ እኛን ባዶ ለማድረግ እና ትኩረታችን የተጠመደበትን ነገር ሁሉ ለማስወገድ እግዚአብሔር በሉዓላዊነቱ ሰዎችን፣ ነገሮችን እና ክስተቶችን ይጠቀማል—ሉቃ. 1፡53፤ ማቴ. 5፡6።

ለ. በመለኮታዊው ልጅነት በመብሰል በሙላት ልጆች እንሆን ዘንድ ክርስቶስ በእኛ ውስጥ መሠራቱ ያስፈልጋል—ገላ. 4፡4-5፤ ሮሜ 8፡15፤ ኤፌ. 1፡5፦

1. ዳግም ከተወለድንበት ጊዜ ጀምሮ፣ የእርሱ መልክ ይኖረን ዘንድ ጌታ በውስጣችን እየሠራ ነው—2 ቆሮ. 3፡18፤ ሮሜ 8፡29።
2. ጌታ ሙሉ በሙሉ መልኩን ወደ እኛ ውስጥ ሲሠራ እና ሙሉ በሙሉ በእኛ በኩል ሲገለጥ፣ በሕይወት የበሰልን እንሆናለን—ኤፌ. 3፡16-17።

ሐ. በአዲስ ኪዳን ጥቅም ላይ እንደዋለው፣ *ብስለት* የሚለው ቃል አማኞች ዳግም በተወለዱ ጊዜ በተቀበሉት ሕይወት በሙላት ማደጋቸውን፣ መብሰላቸውን እና ፍጹም መደረጋቸውን ያመለክታል፦

1. ፈጽሞ በራሳችን የረካን መሆን የለብንም፣ ነገር ግን በክርስቶስ ሕይወት ማደግንና መብሰልን መከታተል ይገባናል፤ በሺሁ ዓመት መንግሥት ላለው የመጨረሻው የክርስቶስ ድሰታ፣ ከኋላ ያሉትን ነገሮች እየረሳን ከፊት ወዳሉት ነገሮች እየተዘረጋን የክርስቶስን ሙሉ ድሰታ እና እርሱን ማትረፍን በመከታተል ወደ ብስለት መሄድ እና መምጣት ያስፈልገናል—ፊልጵ. 3፡12-15።
2. በመንፈሳዊ ሕይወት ለመብሰል ቅድመ ሁኔታው በመለኮታዊው ሕይወት ያለማቋረጥ ማደግ ነው—ኤፌ. 4፡15።
3. የአማኞች እድገትና በክርስቶስ ሕይወት መብሰል የመጨረሻው ውጤት ወደ ሙሉ እድገት የደረሰ ሰው ነው—እንደ ክርስቶስ አካል ቤተ ክርስቲያን የበሰለ ሰው ወደ መሆን ማደጓ—ቁ. 13።

**III. የጳውሎስ አገልግሎት ግብ ለአንዱ አዲስ ሰው ሰውን ሁሉ በክርስቶስ የበሰለ፣ በሙላት ያደገ አድርጎ ማቅረብ ነው—ቆላ. 1፡28-29፤ 3፡10-11፡-**

ሀ. በ 1፡28 “ፍጹም” ተብሎ የተተረጎመው የግሪኩ ቃል “ሙሉ፣” ወይም “የበሰለ” ተብሎም ሊተረጎም ይችላል።

ለ. የጳውሎስ አገልግሎት ሌሎች እስከ ሙሉ እድገት በክርስቶስ በሙብሰል ፍጹማን እና ሙሉ ይሆኑ ዘንድ ክርስቶስን ወደ ውስጣቸው ማደል ነበር—ኤፌ. 4፡13።

ሐ. ወደ ክርስቶስ ውስጥ ይበልጥ በገባን መጠን፣ እርሱ ይበልጥ ወደ ውስጣችን ይመጣል፤ እርሱ ይበልጥ ወደ ውስጣችን በመጣ መጠን፣ እኛም ይበልጥ ወደ እርሱ ውስጥ እገባለን፤ በሕይወት የምናድገው በዚህ ዑደት ነው—ቆላ. 1፡27-28።

መ. ለኃጢአተኞች ወንጌል በመስበክ እና ከቅዱሳን ጋር ኅብረት በማድረግ ውስጥ ግባችን በሕይወት እንዲበስሉ እና በክርስቶስ ፍጹም ሰው ሆነው እንዲቀርቡ ክርስቶስን ወደ ውስጣቸው ማገልገል ነው—3፡10-11፤ ኤፌ. 4፡13-14።

**IV. ለመነጠቅ ዝግጁ ለመሆን በሕይወት መብሰል ያስፈልገናል—ማቴ. 24፡40-41፡-**

ሀ. መነጠቅ በሕይወት የሆነው የእግዚአብሔር ሙሉ ማዳን ማጠናቀቂያ ደረጃ ነው—የሥጋችን መለወጥ፣ ቤዛነት—ሮሜ 5፡10፤ 8፡23፤ ፊልጵ. 3፡21፡-

1. የተቀበልነው መለኮታዊ ሕይወት ካለው ፍላጎት የተነሣ እና ለጌታ ካለን የፍቅራችን ግለት የተነሣ፣ የጌታን መምጣት የሚጠባበቅ ሕይወትን መከታተል እንሻለን—1 ተሰ. 1፡10፤ 2፡19፤ 3፡13፤ 4፡15፤ 5፡23።
2. ጌታን ስንወድ እና መምጣቱን ስንጠባበቅ ሳለ፣ ወደ ጌታ መገኘት ለመነጠቅ ተስፋ እናደርጋለን—ማቴ. 24፡40-41፤ ሉቃ. 17፡31-36፤ 21፡36።

ለ. የበሰሉ መሆን በአንድ ጀምበር የሚሆን ጉዳይ አይደለም፤ በመገለጡ ለመነጠቅ የበሰልን እንሆን ዘንድ ለጌታ መምጣት ራሳችንን ማዘጋጀት፣ እርሱን መውደድ እና በእርሱ ማደግ ያስፈልገናል—ራእ. 14፡1-5።

ሐ. የብስለት ምልክቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ—ዕብ. 6፡1፡-

1. በሚለውጠን መለኮታዊ ሕይወት መሞላት—ኤፌ. 3፡19።
2. በሕይወት መንገሥ—ሮሜ 5፡17።
3. ጠንካራ ምግብ መብላት መቻል—ዕብ. 5፡12-14።
4. በአስተሳሰባችን ሙሉ ሰው መሆን—1 ቆሮ. 14፡20።
5. የሰማዩ አባታችን ፍጹም እንደሆነ ፍጹማን መሆን—ማቴ. 5፡48።
6. አካሉን ማየት፣ አካሉን ማወቅ፣ በአካሉ ውስጥ እና ለአካሉ መኖር፣ ለአካሉ ግድ መሰኘት እና አካሉን ማክበር—ኤፌ. 4፡13-16።

*© 2023 Living Stream Ministry*